ኪንግደም ሳውድ ዐረቢያ
በእስልምና ጉዳዮች፣ ገንዘብ ስጦታ፣
ዳእዋና መምሪያ ሚንስቴር
የህትመትና ሳይንሳዊ ምርም
ድርጅት

# የኡምራ ሥራዎች

አዘጋጅ

ሙሐመድ ቢን ሷሊሕ አል
ኡሰይሚን
አላህ ምህረት ያድርግላቸው

أعمال العمرة باللغة الأمهرية

በአላህ ስም እጅግ ባጣም አዘኝ እጅግ ርህሩህ በሆነው

ምስጋና ለአላህ ይገባው:: የአላህ የአክብሮት እዝነትና የማክበር ሰላምታ በአላህ መልእክተኛ፣ በቤተሰቦቻቸው፣ በባልደረቦቻቸውና በተከተሏቸው ሁሉ ላይ ይውረድ::

ኡምራ ማለት፣ እሱን አስቦ መሐረም፣ «በካዕባው ዙሪያ»ጡዋፍና «ከሶፋና መርዋ መካከል» ሰእይ ማድረግ እንዲሁም ጸጉርን በሙሉ መላጨት ወይንም ማሳጠር ነው::

መሐረም «ኢሕራም» ማለት የኡምራን ሥራ አስቦ «ነይቶ» መግባትና ሥራውን መጀመር ነው::

ኡምራን ላሰበ ሰው የነብያችን ሱና ለጀናባ እንደሚተጠበው ሁሉ ሰውነቱን መታጠብና የዕጣን እንጨት ዘይትም ሆነ ሌላ ባገኘው ሽቶ ራሱንና ጢሙን መቀባት ሲሆን፣ የዚህ ሽቶ ጠረን ከኢሕራም በኋላ መቆየቱ ምንም አይጉዳውም:: ይህውም በሶሒሃይን «ቡኻሪና ሙስሊም» እንደተዘገበው እናታችን ዓኢሻ እንዲህ ስላሉ ነው: "ነብዩ ሰለላሁ አለይሂ ወሰለም መሐረም«ኡምራ/ሐጅ» በፈለጉ ጊዜ ባገኙት ጥሩ ሽቱ ይቀቡ ነበር፣ ከዚያ በኋላ በራሳቸውና በጢማቸው ላይ የሚስኩን «የሽቶ ዓይነት» ነጸብራቅ አይነበር"::

በኢሕራም ጊዜ መታጠብ ለወንዶች እንዲሁም ለሴቶች በወር አበበና በወሊድ ደምም እንኳን ቢሆኑም ሱና ነው:: ይህውም ነብያችን ሶለላሁ

አለይሂ ወሰለም በሐጀተልወዳዕ «የስንብት ሐጅ» ጊዜ አስማእ ቢንት ዑመይስ «የተባለች ባልደረባቸው» ሙሐመድ ቢን አቡበክር «የተባለውን ልጇዋ»ን ዙል ሑለይፋ «በተባለው ቦታ» ውስጥ በወለደች ጊዜ እንደዚህ በማለት ስለአዘዙዋት ነው፡ “ታጠቢ እንዲሁም በጭኖችህ መካከል ጨርቅ አድርገሽ በመቀነትሽ እሰሪውና ኢሕራም አድርጊ” ሥራቸውን አላህ ይውደድላቸውና ጃቢርን ጠቅሰው ሙስሊም ዘግባውታል፡፡

ከታጠበና ሽቱ ካደረገ በኋላ ደግሞ የኢሕራም ልብሱን ይልበስ፡፡ የኢሕራም ልብስ ለወንዶች ሽርጥና ኩታ ነው፡፡ ሴት ደግሞ ጌጣጌጥን በግልጽ ሳታሳይ የፈለገችውን መልበስ ትችላለች፡፡ ኒቃብና የጅ ጉዋንት መልበስ የለባትም፡፡ ባእድ ወንዶች ዘንድ ግን ፊቷን መሸፈን አለባት፡፡

ከዚያም የፈርድ«ግዴታ የሆነ» ሶላት ጊዜ ከሆነ በወር አበባና በወሊድ ደም ያልሆነ ሁሉ ያን ፈርድ ሶላት ይሰገድ። የፈርድ ሶላት ጊዜ ካልሆነ ደግሞ የውዱን ሱና በመነየት ሁለት ረከዓ ይስገድ።

ሶላቱን እንደጨረሰ «ኡምራውን» ይሐርምና ለበይክ ኡምረተን፣ ለበይክ አላሁመ ለበይክ፣ ለበይከ ላሸሪከ ለከ ለበይክ፣ ኢነልሐምደ ወኒዕመተ ለከ ወልሙልክ ላሸሪከ ለክ ይበል።

ይህ እንግድህ የነብያችን ሶለላሁ አለይሂ ወሰለም ተልቢያ«የለበይክ ዘይቤ» ነው። አንዳንድ ጊዜ ለበይክ ኢላህልሐቂ ለበይክ የሚል ይጨምሩ እንደነበር ተወርቷል።

ለወንዶች በተልቢያ ጊዜ ድመጻቻን ከፈ ማድረግ ሱና ነው። ይህውም አስሳኢብ ቢን ኸላድ የተባሉት

የነብያችን ባልደረባ ሥራቸውን አላህ ይውደድላቸውና ነብያን ሶለላሁ አለይሂ ወሰለም እንዲህ ብላዋል የሚል ሐዲስ ስላወሩ ነው "ጂብሪል ወደኔ መጥቶ በኢህላል«ላኢላህ ኢለላህ በማለት»ና በተልቢያ«ለበይክ በማለት» ጊዜ ድምጻቸውን ከፍ እንዲያደርጉ ባልደረቦቸን አዝ ዘንድ ጠይቆኛል" ሐዲሱን አምስቱም ዘጋቤዎች አስፍረውታል።

ይህውም «በዚህ ጊዜ» ድምጽን ከፍ ማድረግ የአላህ ትእዛዛት ገጽታን እንደማጉላትና ተውሒድን እንደማወጅ ይሆናልና ነው።

ሴቶች ደግሞ በተልቢያም ሆነ በሌላ ዚክር ድምጻቸውን ከፍ ማድረግ የለባቸውም። ምክኒያቱም ሴቶች ሰተር ማለታቸው የተፈለገ ነውና።

ለበይክ አላሁመ ለበይክ የሚለው የተልቢያ አድራጊ ቃል ትርጉም ጌታዬ ሆይ! «የተነሳሁት» ጥሪህን በመቀበልና ትእዛዝህን ለመፈጸም ጽኑ በመሆን ነው:: ማለት ነው:: ይህውም «ከማያምርበት ነገር ሁሉ ጥራት ለሱ ይሁንና»አላህ ባሮቹ ወደ ሐጅ እንዲመጡ በወዳጆቹ ኢብራሂምና ሙሐመድ የአላህ የአክብሮት እዝነትና የማክበር ሰላምታ በነሱ ላይ ይሁንና ልሳን አማካይነት ጥሪ አስተላልፏልና ነው:: “«አልነውም» በሰዎችም ውስጥ በሐጅ ትእዛዝ ጥራ እግረኞች ከየሩቅ መንገድ የሚመጡ ከሲታ ግመሎችም ሁሉ ላይ ሁነው ይመጡሃልና:: ለነሱ የሆኑ ጥቅሞችን ይጣዱ ዘንድ”

«በኡምራ» መሐረም የሚፈልግ ሰው ሥራውን እስከመጨረሻው ከመፈጸም የሚያስተጓጉለው እንደበሽታ ወይም

ሌላ ነገር ያጋጥመኛል ብሎ የፈራ እንደሆነ ኒያ በሚያደርግበት ጊዜ ቅድመ መስፈርት ማስቀመጥ ሱና ይሆንለታል። ኒያውን በሚያደርግበት ወቅት እንደዚህ ይበል «የሚያግድ ነገር ካገደኝ የኢሕራሜ መፈቻ ቦታ በዚያ በታገድኩበት ቦታ ይሆናል» ይህን ማለትም ሥራዎችን እስከመጨረሻው እንዳልፈጽም እንደበሽታ ወይም መዘግየት ወይም ከነሱ ሌላ የሆነ የሚከለክል ነገር የከለከለኝ እንደሆነ እኔ በዚያ ቦታ ኢሕራሜን እፈታለሁ ማለት ነው። ይህም የተባለው ነብያችን ሶለላሁ አለይሂ ወሰለም ከእለታት አንድ ቀን ዱባዓህ ቢንት ዙበይር «የተባለች ያጎታቸው ልጅ» ጋ ሄዱና "ሐጅ ማድረግ አስበሻል ይመስለኛል አይደል? አሏት እሷም በአላህ ይሁንብኝ እኔ ህመም የሚሰማኝ ሁኜ እንጂ ሌላ ነገር አይታየኝም

አለቻቸው አሳቸውም ቅድመ መስፈርት አስቀምጠሽ ሐጀ አድሪጊ ጌታዬ ሆይ የኢሕራሜ መፈቻ ባገድክብኝ ቦታ ነውም በይ አሏት፡፡ «በመቀጠልም» እንደዚህ አሏት በጌታሽ ላይ «ካል ሆነ በስተቀር በማለት» የለየሺው ነግር ሁሉ መብትሽ ነው” «ቡኻሪና ሙስሊም የተስማሙበት» ትክክለኛ ሐዲስ ነው፡፡

ሥራዎቹን እስከመጨረሻው ለመፈጸም የሚያደናቅፈው ነገር በመኖሩ የማይሰጋ ሰውማ ቅድመ መስፈርት ሊያስቀምጥ አይገባም፡፡ ይህውም ነቢያችን ሶለላሁ አለይ ወሰለም ኢሕራም ሲያደረጉ ቅደመ መስፈርት አላስቀመጡም «ሙስሊም በዘገቡት» በሐዲሳቸው ደግሞ “የሐጅ ሥራዎቻቹህን ደንብ ከኔ ውሰዱ”«ተማሩ» ብለዋል፡፡ ደገሞም

ለማንም ሰው በደፈናው ቅድመ መስፈርት አስቀምጥ በለው አላዘዙም፡፡ ዱባዓህ ቢንት ዘበይርን በቅድመ መስፈርት ያዘዙትም ሥራዎቹዋን አስከመጨረሻው ከመፈጸም የሚያሰጋት በሽታ ስለነበረባት ነው፡፡

የ«ኡምራን ሥራ» ሐረመ ሰው የሥራዎቹ ቃላዊ ገጽታ በመሆኑ ተልቢያ«ለበይክ አላሁመ ለበይከ ማለት»ሊያበዛ ይገባል፡፡ በተለይም እንደ ኮረብታ መውጣትና ረባዳ ቦታ መውረድ፣ ሌለት መንጋትና ቀን ምመሽት የተከለከለ ወይም እርም የተደረገ ነገር ለመፈጸም ልቡ ሲያስብና የመሳሰሉ ነገሮችን ያካተቱ የሁኔታና የጊዚያት መለዋወጫ በሆነት ጊዜያት በበለጠ ተልቢያ ሊያበዛ ይገባል፡፡

የኡምራ ተልቢውን«ለበይክ አላሁመ ለበይክ»ከሐረመበት ጊዜ ጀምሮ ጠ ‑ዋፍ እስኪጀምር ደረስ፣ የሐጅን ደግሞ ከሐረመበት ጊዜ ጀምሮ በኢድ ቀን ጀምረተል ዐቀባን እስኪወረውር ድረስ ማቋረጥ የለበትም።

ወደ መካ በተቃረበ ጊዜ የሚችል ከሆነ ከመግባቱ በፊት መታጠብ የነብዩ ሱና ነውና ይታጠብ። ነብያችን ሶለላሁ አለይሂ ወሰለም ወደ መካ ሲገቡ ታጥበው ነበር የሚገቡት።

አብዱላህ ቢን ዑመር የሳቸውንና ያባታቸውን ሥራ አላህ ይውደድላቸውና ነብያችን ሶለላሁ አለይሂ ወሰለም “ወደ መካ ሲገቡ በጥሓእ በሚገኘው በሰንየተል ዑልያ በኩል ነበር የሚገቡት፣ ሲወጡ ደግሞ በሰንየቱሱፍላ ነበር የሚወጡት” ሲሉ ዘግበዋል

በመሆኑም የሐጅ«ወይም የኡምራ» ተጓዥ የሚችል ከሆነ ነብያችን ሶለላሁ አለይሂ ወሰለም በገቡት ቢገባና በወጡበት ቢወጣ ይመረጣል።

ወደ መስጂደልሐራም ደረሶ ቀኝ እግሩን በማስቀደም ሲገባ እንዲህ ይበል፡ ቢስሚላህ ወሶላቱ ወሰላሙ ዓላ ረሱሊላህ፣ አላሁመ ኢግፊር ሊ ዙኑቢ ወፍተሕ ሊ አብዋበ ረሕመቲክ፣ አዑዙ ቢላሂል ዐዚም ወቢወጅሂሂል ከሪም ወቢሱልጧኒሂል ቀዲም ሚነሸይጧኒ ረጂም።

ወደ መካ ሲገባ«ልቅናና ሞገስ ለሱ ይሁንና» አላህ ወደ በይቱላሂል ሐራም ለመድረስ ሁኔታዎችን በማመቻቸት የለገሰበትን ተድላ በማስታወስ አላህን በመፍራት ለሱ ራሱን ዝቅ በማድረግና እሱን በማክበር መግባት ይኖርበታል።

ከዚያም በሐጀረል አስወድ«ጥቁሩ ድንጋይ» ትይዩ ጠዋፍን ለመጀመር ወደ በይቱ«ካዕባው» ይጠጋ:: «በቃሉ» ጠዋፍ ነየተኩኝ አይበል:: ይህ ከነበያችን ሶለላሁ አለይሂ ወሰለም የደረሰን ሱና አይደለምና::

እንዲሁም የኒያ«ሃሳብ» ቦታው ልብ ነውና::

ከዚያም የሚሳካለት ከሆነ ሐጀረል አስወዱን በቀኝ እጁ ይንካ ይሳመውም:: ያን የሚያደረገውም «ልቅናና ሞገስ ለሱ ይሁንና» አላህን ማክበርንና የአላህ መልእክተኛን ሶለላሁ አለይሂ ወሰለም ፈለግ መከተልን አስቦ እንጂ ድንጋዩ ይጠቅማል ወይም ይጎዳል በሚል እምነት መሆን የለበትም:: እንደዚያ የሚደረገው «ልቅናና ሞገስ ለሱ ይሁንና» ለአላህ «አክብሮት» ነው::

የምእምናን ልኡል«መሪ» «ዑመር ቢን እለኸጣብ» ሥራቸውን አላህ ይውደድላቸውና ድንጋዩን በሚስሙበት ወቅት “እኔ አንተ ልትጎዳም ሆነ ልትጠቅም የማትችል ድንጋይ መሆንህን ጠንቅቄ አውቃለሁ የአላህ ምልእክተኛ ሶለላሁ አለይሂ ወሰለም ሲስሙህ ባላየሁ ኖሮ እኔ ባልሳምኩህ ነበር” ጀመዓዎች «ስስድስቱም ዘጋቢዎች» አስፍረውታል፡፡

«ድንጋዩን መሳም» የማይሳካለት ከሆነ በእጁ ይንካውና እጁን ይሳም፡፡ «አብደላህ» ኢብን ዑመር የሳቸውንና የአባታቸውን ሥራ አላህ ይውደድላቸውና ድንጋዩን በእጃቸው ነክተው ከዚያም እጃቸውን ስመው ነብያችን እንደዚህ ሲያደርጉ ካየሁበት ጊዜ ጀምሮ እንደዚህ ማድረጌን ትቼ አላውቅም ማለታቸው

በሱሒሐይን«ቡኻሪን ሙስሊም» ተዘግቧል፡፡

«ድንጋዩን» በእጁ መንካት ካልተሳከለት በራሱና በሌሎችም ችግር ሊፈጥር ይችላልና ተጋፍቶ ለመድረስ አይሞክር፡፡ አንዳንድ ጊዜ «በእንደዚህ ዓይነቱ ግፊያ ምክኒያት» በሚደርሰው ጉዳት የአላህ ፍራቻ ይወገድና ጡዋፍን ከተደነገገበት ከአላህ አገልግሎት መስመር ውጭ ያደርገዋል፡፡ አንዳንዴም ትርፍ ንግግር፣ ጭቅጭቅና ጥል ይፈጠራል፡፡

«በዚህን ጊዜ» ከሩቅም ቢሆን «ወደ ድንጋዩ» በእጁ ማመልከት ይበቀል፡፡

«አብዱላህ» ኢብን አባስ የሳቸውንና የአባታቸውን ሥራ አላህ ይውደድላቸውና ነብያችን ሶለላሁ አለይሂ ወሰለም አንድ ጊዜ ግመል ተቀምጠው በበይቱ«በካዕባው» ጡዋፍ

ሲያደርጉ «ድንጋዩ ባለበት» ማእዘን ሲደርሱ ወደሱ በእጃቸው ያመለክቱ ነበር ማለታቸውን ቡኻሪ ዘግበዋል፡፡

በሌላ ዘገባ ደግሞ ይዘውት በነበረ አንድ ነገር ወደሱ አመልክተው አላህ አክብር ብለዋል የሚል ተገኝቷል፡፡

ከዚያም በይቱን«ካዕባውን» በግራው በኩል አድርጎ ወደቀኝ በኩል ይጓዝ ወደ የማኒ ማእዘን ሲደርስ የሚችል ከሆነ ያለ መሳም በእጅ ይንካው፡፡ ካለተቻለ ደግሞ መጋፋት የለበትም፡፡

ከበይቱ«ካዕባው»ከሐጀረል አስወድና ከሩክነል የማኒ ሌላ በእጅ የሚነካው ክፍል የለም፡፡ አነሱ ከ«ነብዩ» ኢብራሂም ግንባታ መሰረት በመሆናቸውና ነብያችን ሶለላሁ አለይሂ ወሰለም ያለነሱ ሌላን «ክፍል በካዕባው» በእጃቸው ያልነኩ በመሆናቸው ነው፡፡

ኢማሙ አሕመድ ሙጃሂድ «አብዱላህ» ኢብን አባስ እንዲህ አሉ ማለታቸውን ጠቅሰው የሚከተለውን ዘገባ አስፍረዋል፡፡ አንድ ወቅት ኢብን አባስ ከሙዓዊያ ጋር በበይቱ«ካዕባው» ጡዋፍ በሚያደርጉ ጊዜ ሙዓዊያ የበይቱን ማእዘናት በሙሉ በእጃቸው መንካት ያዙ፡፡ ያን ጊዜ ኢብን አባስ ለምን እነዚህን ሁለት ማእዘናት በእጅህ ትነካለህ ነብያችን ሶለላሁ አለይሂ ወሰለም በእጃቸው ይነኳቸው አልነበረም? ሲሉ ጠየቋቸው፡፡ ሙዓዊያም ከበይቱ«ካዕባው» ቸል የሚባል «ክፍል» የለም በማለት መለሱ፡፡ ኢብን አባስ ደገሞ "ለናንተ በአላህ መልእክተኛ መልካም መከተል አላችሁ" አሉ«ና ነቀፌታቸውን ገለጹ» ከዚያም ሙዓዊያ«በመጨረሻ» ውነት ተናገርህ ትክክል ነህ አሉ፡፡

ከሩንክነል የማኒና ከሐጀረል አስወድ መካከል እንዲህ ይበል “ረበና ኣቲና ፊዱንያ ሐሰነተን ወፊል ኣኺረቲ ሐሰነተን ወቂና ዐዛበ ናር”

በሐጀረል አስወድ በሚያልፍበት ጊዜ ሁሉ አላሁ አክበር በማለት እንዲያለፈው ያድርግ፡፡ ከዚያ ውጭ ያለውን የጡዋፉን ጊዜ በወደደው ዚክር ዱዓእና ቁርአን በመቅራት ሊያሳልፈው ይችላል፡፡ በበይቱ «ካዕባው» ጡዋፍ ማድግ፣ ከሶፋና ከመርዋ መካከል መሮጥና ጀምራዎችን በድንጋይ መወርወር የተደነገጉት የአላህን ትእዛዝ ለመፈጸም እንጂ ለሌላ ነገር አይደለም፡፡

በዚህ «መጀመሪያ ሲገባ በሚያደርገው ማለታችን ነው» ጡዋፍ ለወንዶች ሱና የሚሆነው በመላ ጠ ዋፉ ቀኝ እጁን ማውጣት፣

በመጀመሪያዎቹ ሦስት ዙሮች ማረትረትና በቀሩት አራቱ ደግሞ ያለማረትረት ተራ ጉዞ መጓዝ ነው::

ቅኝ እጁን ማውጣት ማለት የኩታውን ማህል ከ«ቀኝ» ብብት ስር ጫፎቹን ደግሞ በግራ ትከሻው ላይ በማድረግ ቀኝ ትከሻውን መግለጥ ማለት ነው:: ማረትረት ማለት ደግሞ ርምጃዎቹን እጥር እጥር እያደረገ ጉዞውን ማፍጠን ማለት ነው::

ጡዋፍ ማለት በሐጀረል አስወድ ተጀምሮ በዚያው በሐጀረል አስወድ የሚጨረስ «በካዕባው ዙሪያ የሚደረግ» ሰባት ዙር ጉዞ ሲሆን በሒጅር«ኢስማኢል» ግቢ ማለፍ ጠ ዋፉ ትክክለኛ እንዳይሆን ያደርጋል::

ሰባቱን ዙር «ጡዋፍ» ካጠቃለለ በኋላ ወደ መቃሙ ኢብራሂም ጠጋ ብሎ

“ወተኺዙ ሚን መቃሚ ኢብራሂመ ሙሶላ” የምትለዋን አንቀጽ ያንብብ። ከዚያም ከተቻለ ቀረብ ብሎ ካልተቻለ ደግሞ ርቆም ቢሆን ከመቃሙ ጀርባ ሁለት ረከዓ ይስገድ። በፊተኛዋ ረከዓ ከፋቲሓ በኋላ “ቁል ያአዩሀልካፊሩን”ን በሁለተኛዋ ደግሞ አሁንም ከፋተለሓ በኋላ “ቁል ሁላሁ አሐድን”ይቅራ«ያንብብ»

ከዚያም ተምለሶ የሚችል ከሆነ ሐጀረል አስወድን በእጁ ይንካ። የማይችል ከሆነ በእጁ ከሩቅ ማመልከት የለበትም። ከዚያም ሳእይ«ለመሮጥ» ለማድረግ ይውጣ። ወደ ሶፋ በተቃረበ ጊዜ “ኢነሶፋ ወልመርወተ ሚን ሸዓኢሪላህ” የምተለዋን አንቀጽ ይበል። ከዚህ ቦታ ውጭ ይህችን አንቀ ጽ ማለት የለበትም።

ከዚያም ካዕባውን ማየት እስከሚችበት ደረጃ ድረስ ወደ ሶፋ «ኮረብታ» ይውጣ፡፡ ፊቱን ወደ ካዕባው በማዞርና እጆቹን ከፍ በማደረግ አላህን አምስግኖ በፈለገው የዱዓእ ዓይነት ዱዓእ ያድርግ፡፡ በዚህ ቦታ ከሚያደርጉባቸው የነብያችን ሶለላሁ አለይሂ ወሰለም ዱዓዎች የሚከተለው አንዱ ነበር “ላኢላሀ ኢለላህ ወሕደሁ ላሸሪከ ለህ ለሁል ሙልኩ ወለሁል ሐምዱ ወህወ ዓላኩሊ ሸይኢን ቀዲር፣ ላኢላሀ ኢለላህ ወሕደህ አንጀዘ ወዕደህ ወነሶረ ዐብደህ ወህዘመል አሕዛበ ወሕደህ” ከመካከላቸው ሌላ ዱዓእ በማድረግ ይህን ዱዓእ ሦስት ጊዜ ይደጋግመው፡፡

ከዚያም ከሶፋ ወርዶ አስከ አረንጓደው አምድ ድረስ «በተራ እርምጃ» ይሂድ፡፡ ከሱ«አረንጓደው

አምድ» ሲደርስ የተቻለውን ያህል ከሁለተኛው አረንጓዴ አምድ እስኪደርስ ደረስ ይፍጠን፣ ነገር ግን በሰዎች ላይ ጉዳት ያለማድረስ መሆን አለበት፡፡ ከዚያም ወደ መርዋ እስኪደርስ በተራ እርምጃ ይጓዝ፡፡ ከዚያም መርዋ ላይ ወጥቶ ፊቱን ወደ ካዕባ አዙሮ እጆቹን ከፍ በማደረግ ሶፋ ላይ ያደረገውን ዓይነት ዱዓእ ያድርግ፡፡

ከዚያም ከመርዋ ይውረድና በተራ መጓዚያው ቦታ የተራ ጉዞ በመፍጠ ኛው ቦታ ደግሞ የፍጥነት ጉዞ እያደረገ አንደገና ወደ ሶፋ ይሂድ፡፡ ሶፋ ላይ ወጥቶ ፊቱን ወደ ካዕባ አዙሮ እጆቹን ከፍ በማድረግ በመጀመሪያ «ሶፋ ላይ ሲወጣ»እንዳደረገው ያድርግ፡፡ በቀሪው የሳእይ ጉዞው የወደደው

ዚክር ቁርኣን መቅራትና ዱዓእ ማድረግ ይችላል።

ሶፋና መርዋ ላይ መውጣት እንዲሁም ከሁለቱ ምልክቶች መካከል በፍጥነት መሮጥ ሁሉም ሱና እንጂ ግዴታ«ዋጂብ» አይደሉም።

ከሶፋ አስከመርዋ አንድ ዙር ከመርዋ እስከ ሶፋ ደግሞ ሌላ ዙር የሆነውን ሰባት ዙር ሳእዩን«ሩጫውን» ሲጨርስ ወንድ ከሆነ ጸጉሩን ይላጭ ወይም ያሳጥር። መላጨት ይመረጣል። ነገር ግን ሙተመቲዕ ሁኖ የሐጅ ጊዜ በጣም ቅርብ በመሆኑ ጸጉሩ እንደገና መብቀል የማይችል ከሆነ በዚህን ጊዜ ጸጉሩ ቆይቶለት በሐጅ እንዲላጨው ማሳጠር ይመረጣል። ይህውም ነብያችን ሶለላሁ አለይሂ ወሰለም በዙልሒጃ አረታኛ ቀን ማለዳ ወደመካ በደረሱ ጊዜ ባልደረቦቻቸው ከኢሕራማቸው እንዲፈቱና

ጸጉራቸውን እንዲያሳጥሩ አዘዋቸዋልና ነው።

ሴት ከሆነች ደግሞ በቅንጥና ቅንጧ በኩል የጣት ጫፍ ያህል ጸጉር በመቁረጥ ታሳጥር እንጂ በማንኛውም ሁኔታ ጸጉሯን መላጨት የለባትም።

«ለወንዶች»መላጨት ስንል መላ ጸጉሩን መላጨት ማለታችን ነው። ይህውም ታለቁ አላህ "ጸጉራችሁን የላጫችሁ ስትሆኑ" ስለአለና ነብያችን ሶለላሁ አለይሂ ወሰለም ሙሉ ራሳቸውን ስለተላጩ እናም "የሥራዎቻችሁን ደንቦች ከኔ ተማሩ"በማለታቸው ነው።

እንዲሁም በሚያሳጥርበት ጊዜ መላ ጸጉሩን ሊያሳጥር ይገባል።

እነዚህን ሥራዎች በሚፈጽምበት ጊዜ ኡምራው የተሟላ ይሆናል ከኢሕራሙም ሙሉ በሙሉ ይፈታል፡፡ በኢሕራሙ የተከለከሉ ነገሮች ሁሉ ይፈቀዱለታል፡፡

የኡምራ ሥራዎች በአጭሩ

1. ለጀናባ እንደሚታጠብ ሁሉ ሰውነቱን መታጠብ፡፡

2. የኢሕራም ልብስን መለበስ፡፡ እሱም ለወንድ ሽርጥና ኩታ፣ ለሴት ደግሞ የተፈቀደ ማንኛውም ልብስ ነው፡፡

3. እስከ ጡዋፍ ደረስ ያለማቋረጥ ተልቢያ ማድረግ«ለበይክ አላሁመ ለበይክ ማለት»፡፡

4. በሐጀረል አስወድ ጀምሮ በሱ በመጨረስ በበይቱ «በካዕባው» ሰባት ጊዜ መዞር«ጡዋፍ ማድረግ»፡፡

5. ከመቃሙ«ኢብራሂም» ጀርባ ሁለት ረከዓ መስገድ፡፡

6. በሶፋ ጀምሮ በመርዋ በመጨረስ ሰባት ጊዜ ከሶፋና መርዋ መካከል መሮጥ«ሳእይ ማድረግ»፡፡

7. ወንዶች «ጸጉራቸውን» መላጨት ወይም ማሳጠር፣ ሴቶች ደግሞ ጸጉራቸውን ማሳጠር፡፡

**ኪንግደም ሳውድ ዐረቢያ**

**በእስልምና ጉዳዮች፣ ገንዘብ ስጦታ፣**
**ዳእዋና መምሪያ ሚንስቴር**
**የህትመትና ሳይንሳዊ ምርም**
**ድርጅት**

**መ.ሣ.ቁ**. 61843 **ኮድ** 11478
**ቴሌ**. 00966114736999
**ፋክስ** 00966114737999
**ሪያድ** info@islam.org.sa